በሕዝብ ዘንድ እንዲታወቁና እንዲለመዱ በማሰብ ቤተ ክርስቲያናችን በ፲፱፻፷ (1960)ዎቹ መጀመሪያ ላይ በወቅቱ ታዋቂ በነበረው ክብር ዘበኛ የሙዚቃ ባንድ ጦር በርካታ መዝሙራት በዘመናዊ መሣሪያ ታጅበው እንዲዘመሩ አድርጋ ለምዕመናን ተሰራጭተዋል (2)። እንዲሁም የሙዚቃ ችሎታ ያላቸው ባለሙያዎች በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው መዝሙራትን በዘመናዊ መሣሪያ አጅበው በመጫወት መዝሙራቱ የበለጠ ተወዳጅነትን አትርፈዋል። ይኽንንም ከፍ ያለ አስተዋጽኦ በማየት ቤተ ክርስቲያናችን ለእነዚያ የሙዚቃ መሣሪያ ባለሙያዎች የምስክር ወረቀት በመስጠት ታበረታታ ነበር (3)። ከዚህም የተነሳ አርጋኖን (ኦርጋን) በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ አጃቢ መሣሪያ ሆኖ ቈይቷል። ከዚያ ጊዜ አንሥቶም ፤ እንደ ሊቀ መዘምራን ኪነ ጥበብ እና እንደ መሪጌታ ፀሐይ ብርሃኑ ያሉት ጣእመ ዝማሬያቸው እስከ ዛሬ ድረስ ተሰምቶ የማይጠገበው የቤተ ክርስቲያኒቱ ታዋቂ ልጆችና ሌሎችም በአርጋኖን የታጀቡ መዝሙራትን አዘጋጅተው በካሴት ስላቀረቡ የአማርኛ መዝሙራት ይበልጥ ተወዳጅ እየሆኑ መጡ። እነዚያ በኦርጋን ታጅበው የተዘመሩ መዘሙራት ዛሬም ድረስ ምዕመናኑን ለቃለ ስብከቱ አገልግሎት ይበልጥ ለማዘጋጀት በሀገራችን በየአብያተ ክርስቲያናቱ ይዘመራሉ (4)።

ይህ በእንዲህ እያለ ከ፲፱፻፹ 1980ዎቹ አጋማሽ አንስቶ "በሀገር ባህል መሣሪያ እንጂ ፣ በባእድ መሣሪያ በአርጋኖን መዘመር የለበትም" የሚሉ ወገኖች ተነስተው በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ክፍፍል እንዲነሣ ስላደረጉ ፤ ይህን ችግር ለመፍታት ሲል ቅዱስ ሲኖዶስ በግንቦት ወር ፲፱፻፹፮(1986) ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መሣሪያዎች በአጃቢነት ሥራ ላይ እንዲውሉ ወስኗል፦

**ዋሽንት ፣ ከበሮ ፣ ጸናጽል ፣መሰንቆ ፣በገና ፣እምቢልታ ፣አርጋኖን/ኦርጋን** (5,6) - (ክራር ያልተፈቀደ መሣሪያ መሆኑን እዚህ ላይ ማስተዋል ያሻል)። ኦርጋን ወይም አርጋኖን ማለት ምን ማለት ነው? ስለ ትርጓሜው በተለያዩ መዝገበ ቃላት ላይ የተገለጸውን ይመልከቱ (7)። እነዚህ ኦርጋን የሚለውን ቃል ጆሮአቸው መስማት የማይፈልጉ ተመጻዳቂዎች አባባላቸው ትክክል አለመኾኑን ልቡናቸው እያወቀ ፣ ላለመሸነፍ ብቻ አርጋኖን ማለት አባ ጊዮርጊስ ስለ እመቤታችን ፍቅር የደረሰላት የመጽሐፈ ስም እንጂ መሣሪያ አይደለም እስከ ማለት ደርሰዋል - ታላቅ ትዝብት። በመሠረቱ ቅዱስ ሲኖዶስም መሣሪያ ባይኾን ኖሮ ፤ ከተፈቀዱ መሣሪያዎች እንደ አንዱ አድርጎ ባልቈጠረውም ነበር። ስለዚህ የእነዚህ ሰዎች ክርክር እንዲሁ የአልሸነፍም ባይነት እንጂ ፣ በቂ ማስረጃ ሊያቀርቡለት የማይችሉ በመኾናቸው ተቀባይነትም ፣ አሳማኝነትም አይኖረውም - ፈጽሞ።

አርጋኖን ሲመታ እንደሚመስጠው ድምፅ ጣፋጭ ነው» ይላል ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ። (አርያም ዘቅዱስ ያሬድ የማክሰኞ) (9)

አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫም ቢኾኑ ምስጋናቸውን በአርጋኖንና በሌሎች መሣሪያዎች መስለው ከዚህ እንደሚከተለው ጽፈዋል። የእመቤታችን ምስጋና የሆነውን መጽሐፈ አርጋኖን (10) ሲደርሱ ገና በመግቢያው ላይ «የምስጋና አርጋኖን/ኦርጋን የመዝሙር መሰንቆ እንዚራም የሚባል ይህንን መጽሐፍ እንጀምራለን ይሉና ....የአብ ሙሽራ የኾነችውን (የድንግልን) የምስጋና መጽሐፍ መጻፍ እንድችል እርዳኝ። ለመፈጸምም እንድበቃ ሥልጣኑን ስጠኝ። ከንፈሮቼን እና አንደበቴን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በልዩ ቋንቋ ሰሚዎችን ደስ የሚያሰኝ ነገር ይናገሩ ዘንድ እንደ ኦርጋን/አርጋኖን አድርግልኝ። አንደበቴም እንደ መሰንቆ መልካም ሆኖ ይዘምር ዘንድ ምኡዝ ጣዕም ለዛ ያለው ድምጽ ይሰጥ ዘንድ ድህንፃ መንፈስ/የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደ መሰንቆ አንደበቴን ያጫውተው (ይምታው)። ኦርጋን/አርጋኖን መሰንቆ ሰሚዎቻቸውን ደስተኛ እንደሚያደርጉ እነርሱን የሰሙ በመሣሪያዎቹ ድምጽ እንደሚመሰጡ ይህንን የእመቤታችንን ውዳሴ የሚሰሙ ኅሊናቸው ይማረክ።» (9)

አባ ጊዮርጊስ በተለያየ ስም የተጠሩት መሣሪያዎች ምን ዐይነት ድምጽ እንደሚያወጡና ምን እንደሚመስሉ «እሴብሀ ጸጋኪ» በተባለው ድርሰታቸው ያሉትን ለማስረጃነት እዚህ ላይ መጥቀሱ ተገቢ ይመስለናል። ስለ ***<u>መሰንቆ</u>*** - "ምንት ረባሑ ለመሰንቆ ለእመ አልቦ ዘይሰነቅሖ - የሚሰነቀው የሚገረፈው (የሚሞዝቀው) ከሌለ የመሰንቆ ጥቅሙ ምንድን ነው።» ***<u>እንዚራን</u>*** በተመለከተ ደግሞ «ወምንተ ይደምጽ ንቃወ እንዚራ ዘስቁል ለእመ ኢተነፍሀ በድርግታተ ማኅሌት - (ትርጉም) የተሰቀለው እንዚራ በአንድነት ካልተነፋ የእንዚራ ድምጽ እንዴት ሊሰማ ይችላል?" ብለዋል። (9) እዚህ ላይ <u>የተሰቀለው እንዚራ በአንድነት ካልተነፋ</u> የሚለው አባባል በውጭው ዓለም ታላላቅ ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ፓይፕ ኦርጋን (Pipe Organ) ተብሎ ከሚታወቀው ጋር ተመሳሳይ ነው። የዚህ ዐይነቱ መሣሪያ ድምፅ የሚወጣውም ከፍ ብለው ከተሰቀሉት ከተለያየ ብዙ የቧንቧ ቅርጽ ካላቸው መሣሪያዎች ጋር አንድ ነው። ታዲያ ኦርጋኑ ሲመታ በእነዚያ የቧንቧዎች ቅርጽ ባላቸው ነገሮች ውስጥ አየሩ ሲያልፍ ልዩ የኾነ ማራኪና አስገራሚ የኾነ ድምጽ ያወጣሉ።» እንግዲህ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ስለ ***<u>አርጋኖን</u>*** «በነቀልቃለ ስብሐት ሑኪዮ ለአርጋኖነ ኅሊናየ ከመ ኢያርምም እምስብሐታተ ፍቅርኪ -(ትርጉም) የፍቅርሽን ምስጋና ከማቅረብ አንደበቴ ዝም እንዳይል

አርጋኖን/ኦርጋን ኅሊናዬን {ልቤን} በምስጋና ስሜት ንውጽውጽታ አንቀሳቅሺው/አናውጪው ማለታቸው በነበሩበት ዘመን እንደነዚህ ያሉት መሣሪያዎች በሀገራችን ይታወቁ ስለነበር ማለት ነው።» ኦርጋን በ14ኛው ምእት ዓመት በተለይ በዐፄ እስክንድር ዘመነ መንግሥት በሀገራችን ጥቅም ላይ ውሎ እንደነበር የታሪክ መዛግብት ያስረዱናል። ታዲያ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የቤተ ክርስቲያናችን የዜማ መሥራቾች ምስጋናቸውን በመሣሪያዎች እየመሰሉና እያደነቁ መድረሳቸው መሣሪያዎቹ ለምስጋና የተስማሙ ብቻ ሳይሆኑ ጥቅም ላይ ውለው ቤተ ክርስቲያን ትገለገልባቸው እንደ ነበር ጭምር ይህ አባባላቸው ያስረዳል። ታዲያ እነዚህን መሣሪያዎች ማውገዝና ሽንጥን ገትሮ እሰጥ አገባ ማለት ራስንስ አያስገምትም? መቼም ይህን ለማስተዋል የሮኬት ሳይንቲስት ጭንቅላት አይጠይቅም።

በዚህ በእኛው ዘመን የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፓትርያርክና (ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ) ተከታዮቻቸው በኦርጋን መጠቀምን ፈቀዱ እንጂ አልከለከሉም። እናት ቤተ ክርስቲያናችንም ይኼው እስከዛሬ ስትገለገልበት ቆይታለች። የሆኖ ሆኖ ይህንን ግርግር የፈጠሩት እኒህ የቤተ ክርስቲያኒቷ ተቆርቋሪ ነን ባዮች ከዚያ ጊዜ አንስቶ እስከ እኛ ዘመን የደረሰውን መሣሪያ ለመንቀፍ ፣ በዕውቀትም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወታም ከእነዚህ ቅዱሳን አባቶች እኛ እንበልጣለን ብሎ ወደ ላይ መንጠራራት አይኾንምን??!! ከድፍረትም በላይ ድፍረት። እንግዲህ ለዚህ ለተፈጠረው ችግር ዋናው ምክንያቶች ይህ ራስን አለማወቅና ያላቅም ወደ ላይ መንጠራራቱ ነው - ባጭሩ።

<u>*ጸሐፊው በተከታዩ ርዕስ «ምስጢራዊ ትርጉም ስላላቸው» ይልና ጸናጽልን በተመለከተ እንዲህ በማለት ያብራራል ፤ «ጸናጽሉን ስናይ የያዕቆብን መሰላል ያስታውሰናል። በጸናጽሉ ላይ የምናያቸው ሁለት ቋሚዎች የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን ምሳሌዎች ናቸው። ከላይ የምናየው ደጋን መሰል ቅርጽ ሁለቱን ቋሚዎች ያገናኛቸዋል። በመካከሉም መስቀል ቅርጽ ይደረግበታል ደጋኑም የኖኅ ቃል ኪዳን ምሳሌ ነው። እግዚአብሔር በቀስተ ደመና ስሎ የገባለት ቃል ኪዳን ያስታውሰናል። መስቀሉ ደግሞ ተስፋችን በመስቀሉ እንደተፈጸመ ያስረዳናል። ዘመናውያኑ የዘፈን መሣሪያዎች ግን በዚህ መልኩ ከየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ጋር አይዛመዱም ….. » ይላል።*</u> አሁን እስቲ በማኅሌት ጊዜ መሪጌቶቹ እያዜሙ ጸናጽሉን ሲጸነጽሉ ካህናቱም ይሁኑ ምእምናኑ ይህን ከላይ "<u>በእናንተ በሊቃውንተ ማኅበረ ቅዱሳን</u>" የተዘረዘረውን ምሳሌነት በማስተዋል እያደነቁ ነው ብሎ ማሰብ ይቻላል? ለመኾኑ መጀመሪያውኑ ቅዱስ ያሬድ ተጠቅሞበታል ካልንም እርሱ ስለዚህ መሣሪያ እናንተ እንደምትሉት ስለ ምሳሌነት የተናገረበት ቦታ አለ ወይ? ገና ለገና የኦርጋንን መሣሪያነት ለማንቋሸሽና ለማጣጣል ሲባል እንዲህ ዐይነቱን የድርሳነ ፈጠራ ገለጻ ማቅረብ አእምሮን

